የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 20
ADDIS ABABA-27th January, 2004

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፭/፲፱፻፺፮ ዓ.ም
ለዋቻ-ማጂ የመንገድ ደረጃ የማሳደግ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ............ ገጽ ፪ሺ፭፻፵

## CONTENTS

Proclamation No. 385/2004
African Development Fund Loan Agreement for the Wacha-Maji Road Upgrading Project Ratification Proclamation ............... Page 2540

### አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፭/፲፱፻፺፮

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለዋቻ-ማጂ የመንገድ ደረጃ የማሳደግ ሥራ ፕሮጀክት የሚውል መጠኑ ፳፪ሚሊዮን፯፻፲ሺ ዩ.ኤ (ሃያ ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ አሥር ሺ ዩኒትስ አፍ አካውንት) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፲፫ ቀን ፪ሺ፫ በአቢጃን የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህን የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለዋቻ-ማጂ የመንገድ ደረጃ የማሳደግ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፭/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### PROCLAMATION NO. 385/2004.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

**WHEREAS,** a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provides to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 22,710,000.00 UA (Twenty Two Million Seven Hundred Ten Thousand Units of Account) for financing the Wacha-Maji Road Upgrading Project, was signed in Tunis, on the 13th day of October, 2003;

**WHEREAS,** The House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its session held on the 27th day of January, 2004;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "African Development Fund Loan Agreement for the Wacha-Maji Road Upgrading Project Ratification Proclamation No. 385/2004."

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፲፫ ቀን ፪ሺ፫ በቱኒስ የተፈረመው ቁጥር 2100150007102 የብድር ስምምነት ነው።

## ፫. የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፳፪ሚሊዮን፯፻፲ሺ ዩ.ኤ (ሃያ ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ አሥር ሺህ ዩኒትስ አፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

## 2. Definition

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. 2100150007102 signed in Tunis on the 13th day of October 2003 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund.

## 3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 22,710,000.00 UA (Twenty Two Million Seven Hundred Ten Thousand Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 3. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the 27th day of January, 2004

**Done at Addis Ababa, this 27th day of January, 2004**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**